# NATIONAL LEAD POISONING PREVENTION WEEK

★ ★ ★ WEEK ★ ★ ★

IN THE DISTRICT OF COLUMBIA

# 2021 የመገልገያ ኪምችት

**#LeadFreeKids**

**#NLPPW2021**

**@DOEE_DC**

Lead Free KIDS for a Healthy Future

DEPARTMENT OF ENERGY & ENVIRONMENT

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ብሔራዊ በሊድ መመረዝ መከላከያ ሳምንት (NLPPW) 2021

*እውነታዎችን ያግኙ፣ ቤትዎን ያስመርምሩ፣ ልጅዎን ያስመርምሩ* is የዚህ ዓመት መፈክር ነው፣ ለብሔራዊ በሊድ መመረዝ መከላከያ ሳምንት (NLPPW)፣ ኦክቶበር 24–30, 2021። የከንቲባ ሙሪየል ባውሰር አስተዳደር ግለሰቦች እና ድርጅቶች የሊድ ተጋላጭነትን መፈለግ እና መከላከል በተመለከተ የዲስትሪክት ነሪዎች መካከል ግንዛቤ ለመፍጠር ይህን ጥረት እንዲቀላቀሉ ያበረታታል።

በሊድ መመረዝ በዲስትሪክቱ ውስጥ ከባድ የጤና ስጋት ሆኖ ቀጥሏል፣ እና ከ6 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች በጣም ተጋላጭ ናቸው። በሊድ-ለተበከለ ቀለም፣ አዋራ፣ አፈር፣ ወይም ውሃ የተጋለጡ ልጆች በመማር፣ ባህርይ፣ እና እድገት ላይ ዘላቂ ችግሮች ሊያጋጥሟቸው ይችላል።

መልካም ዜና ምንድን ነው? በሊድ መመረዝን መከላከል ይቻላል።

እንዴት መርዳት ይችላሉ? ስለ ሊድ ምርመራ እና መከላከል አስፈላጊነት ለሌሎች ግንዛቤ ለመፍጠር ይህን የመገልገያ ክምችት ይጠቀሙ፥

- **እውነታዎቹን ያግኙ።** እራስዎን እና ቤተሰብዎን ከሊድ ተጋላጭነት እንዴት መከላከል እንደምችሉ ይማሩ። ይጎብኙ doee.dc.gov/service/lead-and-your-health።
- **ቤትዎን ያስመርምሩ።** በዲስትሪክቱ የሊድ ህግ ስር መብቶችዎን እና በቤቱ ውስጥ ሊድ-ላይ የተመሰረተ የቀለም አደጋዎችን ለመለየት የሊድ ተቆጣጣሪ ወይም የስጋት ገምጋሚን እንዴት መቅጠር እንደምችሉ ይወቁ። ሲያድሱ፣ ለዲስትሪክቱ የቀረበውን ከሊድ-ነጻ የሥራ ልምምዶችን እና መስፈርቶችን ይከተሉ። የበለጠ ለማወቅ፣ ይጎብኙ doee.dc.gov/lead።
- **ልጅዎን ያስመርምሩ።** ልጅዎ ለሊድ እንደተጋለጠ/ች ለማወቅ ቀላል የደም ምርመራ ብቸኛው መንገድ ነው። ሁሉም ትናንሽ ልጆች ለሊድ እንድመረመሩ የዲስትሪክት ህግ ይጠይቃል። ሀኪምዎ ልጅዎን በ 6 እስከ 14 ወራት፣ እና እንደገና በ 22 እስከ 26 ወራት እድሜ ለሊድ እንዲመረምር ይጠይቁ። ለማስታወስ ቀላል መንገድ፥ እያንዳንዱን ህጻን፣ በሁለት ሁለት ጊዜ ይመርምሩ። የበለጠ ለማወቅ፣ ይጎብኙ doee.dc.gov/twicebytwo።

ይህ የመገልገያ ክምችት ስለ ሊድ ማጣራት እና መከላከል አስፈላጊነት ወላጆችን፣ አያቶችን፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎችን፣ አካራዮችን፣ ኮንትራክተሮችን፣ የንብረት አስተዳዳሪዎችን፣ አስተማሪዎችን፣ እና ሌሎችን ለማስተማር በስራ ቦታዎ፣ የአምልኮ ቦታዎ፣ ትምህርት ቤት፣ ንግድ ቦታ፣ እና የጤና እንክብካቤ ተቋም ውስጥ ለመጠቀም የሚያስችሉ የናሙና መልዕክቶችን፣ ቁሳቁሶችን፣ እና ሌሎች መገልገያዎችን ያቀርባል።

የ U.S. በሽታን የመቆጣጠር እና መከላከል ማእከል (CDC)፣
የU.S. የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ (EPA)፣ የU.S. መኖሪያ ቤት እና የከተማ እድገት መምሪያ (HUD)፣ እና አጋሮቻቸውን በNLPPW ውስጥ ባሳዩት አመራር በጣም እናመሰግናለን። በዚህ መገልገያ ክምችት ውስጥ ያሉ የተወሰኑ የናሙና ቁሳቁሶች ከNLPPW የመገልገያ ቋቁሶች የተገኙ ሲሆኑ በ CDC፣ EPA፣ እና HUD የተዘጋጁ ናቸው።



GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ያለው NLPPW

የባውሰር አስተዳደር፣ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሀይል እና የአካባቢ ጥበቃ መምሪያ (DOEE) አማካኝነት፣ በመላው የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የተደራሽነት ስራዎች ጋር በተያያዘ NLPPWን እያመለከተ ነው።

ከእሁድ፣ ኦክቶበር 24 እስከ ቅዳሜ፣ ኦክቶበር 30፣ 2021፣ DOEE በማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት ትምህርታዊ ተደራሽነትን ያከናውናል እና የNLPPW ዌብናር እንቅስቃሴዎችን በ U.S. መኖሪያ ቤት እና የከተማ እድገት (HUD)፣ በ U.S. የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ (EPA)፣ እና በሽታን የመቆጣጠር እና መከላከል ማእከል (CDC) የሚዘጋጁትን ያስተዋውቃል። እንዲሁም DOEE ከ D.C. የጤና እንክብካቤ ፋይናንስ ጋር በአጋርነት ይሰራል፣ ለሊድ ማጣራት እና ሪፖርት ማድረግ የዲስትሪክቱ መስፈርቶች ላይ




ዓመታዊ ማስታወሻዎችን ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ማቅረብ ላ

ከ DOEE ጋር በ NLPPW እንቅስቃሴዎች ላይ አጋርነት ለመፍጠር ፍላጎት ካሉዎት፣ ጊፍት አቦይት- ዩክፑሎን በ (202) 535-2264 ወይም gift.oboite@dc.gov ያነጋግሩ።

## የመገልገያ ክምችት ይዘቶች


- የNLPPW ዌብናር ፕሮግራም ........ 3
- የኢሜይል ስርጭት/የጋዜጣ ጽሁፍ/የሃይማኖታዊ አገልግሎት መጽሔት ........ 4
  - ናሙና #1፥ ብሔራዊ የሊድ መመረዝ መከላከል ሳምንት ነው! ........ 4
  - ናሙና #2፥ ልጅዎን ለሊድ ለመመርመር ሀኪምዎን ይጠይቁ........ 5
- የናሙና ማህበራዊ ሚዲያ ልጥፎች........ 6
- የናሙና ጋዜጣዊ መግለጫ ........ 9
- የኢንተርኔት መገልገያዎች........ 10

# የNLPPW ዌብናር ፕሮግራም

ኦክቶበር 24-30፣ 2021
ብሔራዊ የሊድ መመረዝ መከላከል ሳምንት 2021 ነው

ከሊድ ነጻ ህጻናት ለጤናማ መጪ ጊዚ

እውነታዎቹን ያግኙ
ቤትዎን ያስመርምሩ
ልጅዎን ያስመርምሩ




ወደ NLPPW ዋና ገጽ ለመሄድ እዚህ ይጫኑ

የ NLPPW የዌብናር ተከታታይ ቪድዮዎች ዝርዝሮችን እና መመሪያዎች ለማውረድ እዚህ ይጫኑ

# ናሙና #1፥ የኢሜይል ስርጭት/የጋዜጣ ጽሁፍ/የሃይማኖታዊ አገልግሎት መጽሔት

**ብሔራዊ የሊድ መመረዝ መከላከል ሳምንት ነው!**

የዚህ ዓመት ብሔራዊ የሊድ መመረዝ መከላከል ሳምንት መፈክር፣ "እውነታዎችን ያግኙ፣ ቤትዎን ያስመርምሩ፣ ልጅዎን ያስመርምሩ፣" ወላጆች በአካባቢያቸው ውስጥ የልጆች ለሊድ ተጋላጭነትን መቀነስ የሚችሉባቸውን በርካታ መንገዶች ላይ ትኩረት ይሰጣል። ሊድ ከባድ የጤና ችግሮችን ማምጣት የሚችል ብረት ነው፣ በተለይ ወጣት ልጆች ውስጥ። የሊድ ተጋላጭነት የልጅ አንጎል እና የሌሎች ወሳኝ አካላት መጎዳትን ሊያስከትል ይችላል። እንዲሁም የእድሜ ልክ የመማር እና የባህርይ ችግሮችን መፍጠር ይችላል።

በጣም የተለመደ የሊድ ተጋላጭነት ምንጭ ሊድ-ላይ የተመሰረተ ቀለም መሆኑን ያውቁ ነበር? ከ 1978 በፊት የተገነባ ቤት ብዙውን ጊዜ በሊድ የተሰራ ቀለም አለው። በጣም የተለመዱ የቤተሰብ ሊድ አደጋዎች የሚያካትቱት፥

- መደበኛ የሚከፈቱ እና የሚዘጉ ነገሮች፣ ለምሳሌ፣ ያረጁ መስኮቶች እና በሮችን መክፈት እና መዝጋት ቀለሙን መሰባበር እና መፋቅ ይችላል እና የሊድ አዋራን መፍጠር ይችላል።
- ልጆች ንፋስ ላይ ያለውን የሊድ አብዋራ ወደ ውስጥ መተንፈስ ይችላሉ።
- እንዲሁም ልጆች የሊድ አብዋራ የተሰበሰበበት የመስኮት ደፍ፣ አሻንጉሊቶች፣ ወይም ሌሎች ስፍራዎችን ከነኩ ወይም ካኘኩ በኋላ እጆቻቸውን በአፋቸው ውስጥ ሲያስገቡ የሊድ አቧራን መዋጥ ይችላሉ።

በቤትዎ ውስጥ ቤተሰብዎን ሊድ-ላይ ከተመሰረቱ የቀለም አደጋዎች መጠበቅ ውስጥ ለመርዳት ቀላል እርምጃዎችን መውሰድ ይችላሉ፥

- የልጆች እጆችን እና መጫወቻዎችን በተደጋጋሚ ያጥቡ እና ወለሎችን፣ የመስኮት ደፍ፣ እና ሌሎች ስፍራዎችን በእርጥብ ጨርቅ ወይም እርጥብ መጥረጊያ ያጽዱ።
- እግሮችዎን በምንጣፍ ላይ ይጥረጉ ወይም ወደ ቤትዎ ከመግባትዎ በፊት ጫማዎን ያውልቁ።
- ቤትዎን ቀለም ለመቀባት፣ ለመጠገን፣ ወይም እንደገና ለመስራት በሊድ-ነጻ የሥራ ልምምዶች የሰለጠኑ ምስክር ወረቀት ያላቸው ባለሙያዎችን ብቻ ይጠቀሙ።

እንዲሁም ሊከሰት ለሚችል ተጋላጭነት ልጅዎን በሀኪም ማስመርመር አስፈላጊ ነው። ልጅዎን ያስመርምሩ ቢያንስ ሁለት ጊዜ፣ከ 6 ወራት እና 14 ወራት እድሜ እና ከ 22 እና 26 ወራት እድሜ መካከል። የበለጠ ለማወቅ፣ ይጎብኙ [doee.dc.gov/lead](doee.dc.gov/lead)።



GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# ናሙና #2፥ የኢሜይል ስርጭት/የጋዜጣ ጽሁፍ/የሃይማኖታዊ አገልግሎት መጽሔት

**ልጅዎን ለሊድ ለመመርመር ሀኪምዎን ይጠይቁ**

በሊድ የተመረዙ ብዙ ህጻናት የታመሙ አይመስሉም ወይም እንደታማሚ አይሆኑም። ነገር ግን የሊድ ተጋላጭነት የወደ ፊት የጤና፣ የባህርይ፣ እና የመማር ችግሮችን ማስከተል ይችላሉ።

ልጅዎ ለሊድ እንደተጋለጠ/ች ለማወቅ የደም ምርመራ ብቸኛው መንገድ ነው።

**ልጅዎ እንዲመረመር/እንድትመረመር ያድርጉ!**

በሕግ፣ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የሚኖሩ ሁሉም ህጻናት

በ **6–14 ወራት** እና **22–26 ወራት** እድሜዎች ለሊድ መመርመር አለባቸው።

የልጅዎ የሊድ ደረጃ ከፍተኛ ከሆነ፣ ሀኪምዎ ልጅዎን ከተጨማሪ የሊድ ተጋላጭነት መጠበቅ የሚያስችሉ መንገዶችን ለመለየት ማገዝ እና እንዳስፈላጊነቱ ህክምናን ማቅረብ ይችላል።

የበለጠ ይማሩ በ፥ doee.dc.gov/twicebytwo።



Lead Free KIDS for a Healthy Future
DEPARTMENT OF ENERGY & ENVIRONMENT
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# ማህበራዊ ሚዲያ፥ ትዊተር እና ፌስቡክ

1. ብሔራዊ የሊድ መመረዝ መከላከል ሳምንት ነው በዲሲ ውስጥ! ልጅዎን ያስመርምሩ እና እውነታዎቹን ያግኙ! doee.dc.gov/twicebytwo #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC
2. ያውቁ ኖሯል? በሕግ፣ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የሚኖሩ ሁሉም ህጻናት በ 6–14 ወራት እና 22–26 ወራት እድሜዎች ሁለት ጊዜ መመርመር አለባቸው። doee.dc.gov/twicebytwo #NLPPW2021 @DOEE_DC
3. ያውቁ ኖሯል? የደም ምርመራ የሊድ መመረዝ የሚታይበት ብቸኛው መንገድ ነው? የልጅዎ ሀኪም ልጅዎን ለሊድ እንዲመረምር መጠየቅን ያስታውሱ። #NLPPW2021 @DOEE_DC
4. ወላጆች – የህጻናት ሀኪምዎ የልጅዎን ደም ለሊድ እንዲመረምር ይጠይቁ። እርሱም ለማወቅ ብቸኛ መንገድ ነው። doee.dc.gov/twicebytwo. #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC
5. እድሜያቸው ከ6 ዓመት በታች የሆነ ልጆች ለሊድ መመረዝ በጣም ተጋላጭ ናቸው። የበለጠ ይማሩ፥ doee.dc.gov/service/lead-and-your-health. #NLPPW2021 @DOEE_DC
6. በቦታዎ ላይ ስራ እያሰሩ ነው? የቤትዎን ማሻሻሎች በልጅ ያረጋግጡ፥ doee.dc.gov/node/1279221. #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC
7. እያሳደሱት ነው? በ DOEE-የተረጋገጠ የሊድ ባለሙያ ብቻን ይቅጠሩ። ዝርዝር ይህ ነው፥ doee.dc.gov/node/20762. #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC
8. ቤትዎን ከመግዛት፣ ከማከራየት፣ ወይም ማሳደስ በፊት፣ ሊድ-ላይ ለተመሰረተ ቀለም እንዲታይ ያድርጉ፥ doee.dc.gov/node/1279221. #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC
9. ስለ ሊድ ተጨንቀዋል? በጥያቄዎች ብሔራዊ የሊድ መረጃ ማእከል ያነጋግሩ በ 1-800-424-LEAD or bit.ly/2aOFXU8. #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC
10. የዛሬ ቀን ምክር፥ በትክክል ያሳድሱ! በቤትዎ ውስጥ ስራ እንዲሰሩ ትክክለኛ ሰዎችን እንደቀጠሩ ያረጋግጡ! ይህ እንዴት እንደሚሆን ነው፥ doee.dc.gov/node/1279221
11. ያውቁ ኖሯል? እንደ ተከራይ፣ የሊድ ደህንነት በተመለከተ መብቶች አሉዎት? #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC. የበለጠ ይማሩ፥ doee.dc.gov/node/7952
12. ያውቁ ኖሯል? እንደ አካራይ፣ ማንኛውም ሊድ-ላይ የተመሰረተ ቀለም አደጋዎችን ለተከራዮችዎ ማሳየት አለብዎት። #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC የበለጠ ይማሩ፥ doee.dc.gov/node/8022
13. ያውቁ ኖሯል? በተወሰኑ ኢንደስትሪዎች ውስጥ የሚሰሩ ወላጆች ሊድን ከስራ ቦታ ወደ ቤት ሊያመጡ ይችላሉ። ገላዎን ይታጠቡ፣ ልብሶችዎን ይቀይሩ፣ እና ጫማዎን ይጥረጉ። #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC Learn more፥ cdc.gov/nceh/lead/tips.htm
14. የዛሬ ቀን ምክር፥ "በትክክል ያሳድሱ" የሊድ ተጋላጭነት ስጋትን ለመቀነስ። #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC How? የ DOEE የምክር ገጽን እዚህ ያውርዱ፥ doee.dc.gov/publication/renovate-right-tip-sheet-preventing-lead-exposure



Lead Free KIDS for a Healthy Future
DEPARTMENT OF ENERGY & ENVIRONMENT
WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# ማህበራዊ ሚዲያ፥ ትዊተር እና ፌስቡክ (እንግሊዘኛ)

1. It's National Lead Poisoning Prevention Week in DC! Get your child tested and get the facts! doee.dc.gov/twicebytwo #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC
2. Did You Know? By law, every child in the District must be tested twice, at 6-14 months and 22-26 months of age. doee.dc.gov/twicebytwo #NLPPW2021 @DOEE_DC
3. Did You Know? A blood test is the only way to check for lead poisoning? Remember to ask your child's doctor to test your child for lead. #NLPPW2021 @DOEE_DC
4. Parents – ask your pediatrician to test your child's blood for lead. It's the only way to know. doee.dc.gov/twicebytwo. #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC
5. Children under 6 years of age are most at risk for lead poisoning. Learn more: doee.dc.gov/service/lead-and-your-health. #NLPPW2021 @DOEE_DC
6. Having work done on your place? Childproof your home improvements: doee.dc.gov/node/1279221. #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC
7. Renovating? Hire only DOEE-certified lead professionals. Here's a list: doee.dc.gov/node/20762. #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC
8. Before buying, renting, or renovating your home, have it checked for lead-based paint: doee.dc.gov/node/1279221. #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC
9. Worried about lead? Contact the National Lead Information Center with questions at 1-800-424-LEAD or bit.ly/2aOFXU8. #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC
10. Tip of the Day: Renovate Right! Make sure you've hired the right folks to do work in your home! Here's how: doee.dc.gov/node/1279221
11. Did you know? As a tenant, you have rights regarding lead safety? #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC. Find out more: doee.dc.gov/node/7952
12. Did you know? As a landlord, you must disclose any lead-paint hazards to your tenants. #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC Find out more: doee.dc.gov/node/8022
13. Did you know? Parents in certain industries may bring lead home from work. Shower, change your clothes, and wipe your shoes. #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC Learn more: cdc.gov/nceh/lead/tips.htm
14. Tip of the Day: "RENOVATE RIGHT" to reduce the risk of lead exposure. #leadfreekids #NLPPW2021 @DOEE_DC How? Download the DOEE tip sheet here: doee.dc.gov/publication/renovate-right-tip-sheet-preventing-lead-exposure

# በአካባቢ ውስጥ ያለ ሊድ፥ ማህበራዊ ሚዲያ

82
**Pb**
Lead 207.2

## ሊድ

### ሊድ

በአካባቢ ውስጥ ያለ ሊድ፥ ሊድ በተፈጥሮ የሚገኝ ነው፤ በአካባቢያችን ሁሉም አካላት ውስጥ ሊገኝ ይችላል። በሊድ-የተበከሉ አቧራ እና ቅንጣት ነገሮች በአየር፣ አፈር፣ ውሃ ውስጥ፣ ወይም ሰዎች የሚራመዱበት እና የሚጫወቱበት የመሬት ስፍራዎች ላይ መገኘት ይችላሉ። ሊድ ስዋጥ፣ መርዘኛ እና ለሰዎች ጎጂ ነው፣ በትንሽ መጠን ብሆንም እንኳ።

እቤት ውጪ፣ ልጆች ጥሬ አፈር አካባቢ የአትክልት ጓሮ ውስጥ ወይም የተበከለ የመጫወቻ ስፍራዎች ላይ ስጫወቱ ለሊድ ሊጋለጡ ይችላሉ። በአፍር ውስጥ ያለ የተወሰነ ሊድ ከታሪካዊ ሊድ ያለው ጋዝ መጠቀም ይመጣል። አፈር እና የመጫወቻ ስፍራዎች በተጨማሪም ከአቅራቢያ ያሉ ህንጻዎች ውጫዊ ገጽ ላይ ወይም ከህንጻዎች ማሳደስ ወይም መፍረስ በሚመጣ የተሸረሸረ ሊድ-ላይ የተመሰረተ ቀለም ሊበከሉ ይችላሉ።

1. የሊድ ተጋላጭነት የብዙ ከተማ አካባቢዎች ከባድ ውርስ ነው፣ በአካባቢው ውስጥ ያሉ የሊድ ምንጮችን በመረዳት፣ በመለየት፣ እና ደህንነት ባለው ሁኔታ በማስወገድ፣ የሁሉም ኗሪዎቻችን የረጅም ጊዜ ጤናን ማረጋገጥ ውስጥ መርዳት እንችላለን። #NLPPW2021 #leadfreekids

2. በክፍት አፈር እና የመጫወቻ ስፍራ ቁሳቁሶች ላይ ሲሆኑ እንደ መብላት እና መጠጣት ያሉ ከእጅ ወደ አፍ ንክኪዎችን መከላከል። ማንኛውም የመጫወቻ ቦታ ቁሳቁሶችን በአፍዎ ውስጥ አያስገቡ። #NLPPW2021 #leadfreekids

3. ልጆች እጆችቻቸውን እና ፊታቸውን በሰሙና እና ውሃ እንዲታጠቡ፣ እና ጥሬ አፈር ያለባቸው የመጫወቻ ቦታዎችን ወይም ሌሎች ስፍራዎችን ለቀው ሲወጡ ጫማቸውን እንዲጠርጉ ማረጋገጥ። #NLPPW2021 #leadfreekids

4. በግልጽ የቆሸሹ ልብሶችን በጥንቃቄ ያውልቁ እና ያጥቡ፤ በተዘጉ ክፍሎች ውስጥ አቧራዎችን ከልብሶች አያራግፉ። #NLPPW2021 #leadfreekids

5. የተበከለ አፈርን ወደ ቤትዎ መሄድን ያስወግዱ። ቤትዎን ስትገቡ ሁሉም ሰው ጫማቸውን በር ላይ እንዲተው ያረጋግጡ። #NLPPW2021 #leadfreekids።

6. ቆሻሻን እና አቧራን እንዲስብ የበር ምንጣፍን ሁሉም መግቢያ መንገዶች ውጪ እና ውስጥ ያስቀምጡ። #NLPPW2021 #leadfreekids

7. ሊድ በተፈጥሮ የሚገኝ ነው፤ በአካባቢያችን ሁሉም አካላት ውስጥ ሊገኝ ይችላል። በሊድ-የተበከሉ አቧራ እና ቅንጣት ነገሮች በአየር፣ አፈር፣ ውሃ ውስጥ፣ ወይም ሰዎች የሚራመዱበት እና የሚጫወቱበት የመሬት ስፍራዎች ላይ መገኘት ይችላሉ።#NLPPW2021 #leadfreekids

ሙሉ አካባቢ ውስጥ ያለ ሊድ አንድ-ገጽን እዚህ ያውርዱ



Lead Free KIDS for a Healthy Future
DEPARTMENT OF ENERGY & ENVIRONMENT
WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# የናሙና ጋዜጣዊ መግለጫ

(ለሚዲያ ጥያቄዎች ተጠሪ ሰው ያስገቡ)

**ብሔራዊ የሊድ መመረዝ መከላከል ሳምንት ነው፣ ኦክቶበር 24-30, 2021**

**በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ስለ ሊድ ማጣራት እና መከላከል ግንዛቤ መፍጠር**

በሊድ መመረዝ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ከባድ የጤና ስጋት ሆኖ ቀጥሏል፣ እና ከ6 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች በጣም ተጋላጭ ናቸው። ደህንነት ያለውየሚታወቅ የሊድ ተጋላጭነት ደረጃ የለም። እንደሁም ትንሽ የልጅነት ጊዜ የሊድ ተጋላጭነት የእድሜ ልክ የጤና፣ የመማሪያ፣ እና የባህርይ ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል።

ሊድ-ላይ የተመሰረተ ቀለም እና በሊድ-የተበከለ አቧራ ለልጆች ትልልቆቹ የሊድ ተጋላጭነት ምንጮች ናቸው በዲስትሪክቱ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ቤቶች የተሰሩት ከ 1978 በፊት ነው እና ሊድ-ላይ የተመሰረተ ቀለም አላቸው። እንደ ቀለም ቀቢዎች፣ የጉልበት ሰራተኞች፣ ወይም ኮንትራክቶች ያሉ ሠራተኞች በሥራ ልብሶቻቸው እና ጫማዎቻቸው የሊድ አቧራን ወደ ቤት ማምጣት ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ሊድ በአፈር እና የመጠጥ ውሃ ውስጥ ሊገኝ ይችላል።

ምንም እንኳ ሊድ በአካባቢ ውስጥ በቀጣይነት ቢኖርም፣ በሊድ መመረዝን መከላከል ይቻላል። የሊድ ተጋላጭነትን የመፈለግ እና የመከላከል አስፈላጊነት በተመለከተ በዲስትሪክቱ ውስጥ ግንዛቤ ለመጨመር (የድርጅትዎ ወይም ቡድንዎ ስምን እዚህ ያስገቡ)፣ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሀይል እና የአካባቢ ጥበቃ መምሪያ፣ የበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማእከል፣ የU.S. የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ፣ እና የU.S. መኖሪያ ቤት እና የከተማ እድገት መምሪያ ጋር በመሆን፣ ብሔራዊ የሊድ መመረዝ መከላከል ሳምንት (NLPPW) ውስጥ እየተሳተፈ ነው፣ ኦክቶበር 24–30።

(ስለ ሊድ መመረዝ መከላከል ተግባሮችዎን በተመለከተ አንቀጽ ያስገቡ እና እዚህ ይጻፉ)

የዚህ ዓመት የ NLPPW መፈክር "ከሊድ ነጻ ህጻናት ለጤናማ መጪ ጊዜ" ነው። (የድርጅት ስም ያስገቡ) ቤተሰብዎን ከሊድ ለመጠበቅ ውስጥ ለመርዳት ማድረግ የሚችሉትን ቀላል ነገሮች በተመለከተ መልዕክት እያሰራጨ ነው፥

- **ቤትዎን ያስመርምሩ።** በዲስትሪክቱ የሊድ ህግ ስር መብቶችዎን እና በቤቱ ውስጥ ሊድ-ላይ የተመሰረተ የቀለም አደጋዎችን ለመለየት የሊድ ተቆጣጣሪ ወይም የስጋት ገምጋሚን እንዴት መቅጠር እንደምችሉ ይወቁ። ሲያድሱ፣ ለዲስትሪክቱ የቀረበውን ከሊድ-ነጻ የሥራ ልምምዶችን እና መስፈርቶችን ይከተሉ። የበለጠ ለማወቅ፣ ይጎብኙ doee.dc.gov/lead።
- **ልጅዎን ያስመርምሩ።** ልጅዎ ለሊድ እንደተጋለጠ/ች ለማወቅ ቀላል የደም ምርመራ ብቸኛው መንገድ ነው። ሁሉም ትናንሽ ልጆች ለሊድ እንድመረመሩ የዲስትሪክት ህግ ይጠይቃል። ሀኪምዎ ልጅዎን በ 6 እስከ 14 ወራት፣ እና እንደገና በ 22 እስከ 26 ወራት እድሜ ለሊድ እንዲመረምር ይጠይቁ። ለማስታወስ ቀላል መንገድ፥ እያንዳንዱን ህጻን፣ በሁለት ሁለት ጊዜ ይመርምሩ። የበለጠ ለማወቅ፣ ይጎብኙ doee.dc.gov/lead።
- **ስለ መጠጥ ውሃ ይማሩ።** ነጻ የሊድ ምርመራ ኪት ለመጠየቅ፣ የ DC ውሃን በ (202) 612-3440 ወይም leadtest@dcwater.com ያነጋግሩ። ለመጠጣት እና ለማብሰል ቀዝቃዛ ውሃ ብቻ መጠቀምን ያስታውሱ። የበለጠ ለማወቅ፣ ይጎብኙ dcwater.com/lead።

ለተጨማሪ መረጃ፣ ያነጋግሩ (የድርጅትዎን የግንኙነት መረጃን እዚህ ያስገቡ) ለ ብሔራዊ የሊድ መረጃ ማእከል ነጻ የስልክ መስመር በ 1-800-424-LEAD (5323) ይደውሉ።



GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# የኢንተርኔት መገልገያዎች

**ቤተሰቦች**

- ቤተሰብዎን በቤትዎ ውስጥ ከሊድ ይጠብቁ፥ epa.gov/sites/production/files/2017-06/documents/pyf_color_landscape_format_2017_508.pdf
- የሊድ መመረዝን በጤናማ አመጋገብ ይከላከሉ፥ epa.gov/sites/production/files/2014-02/documents/fight_lead_poisoning_with_a_healthy_diet.pdf
- በትክክል ለማሳደስ ከሊድ-ነጻ የተረጋገጠ መመሪያ፥ epa.gov/sites/production/files/documents/renovaterightbrochure.pdf
- ሊድ እና ጤናዎ፥ doee.dc.gov/service/lead-and-your-health

**በቤት ውስጥ ሊድ ላይ እርምጃ መውሰድ የሚችሉባቸው ተጨማሪ መንገዶች፥**

- ሊድ-ላይ የተመሰረተ የቀለም አደገኛ ኬሚካሎችን ለመለየት የሊድ ተቆጣጣሪ ወይም የአደጋ ገምጋሚን ይቅጠሩ። አንድ ያግኙ በ፥ doee.dc.gov/publication/lead-based-paint-consultant-companies።
- ለ DC ውሃ በ (202) 612-3440 ይደውሉ ኢሜይል ይላኩ leadtest@dcwater.com እና በውሃዎ ውስጥ ሊድ እንዳለ ለማወቅ ነጻ የሊድ ምርመራ ኪት ለመጠየቅ።
- ለሊድ ቱቦ መተኪያ እርዳታ ፕሮግራም ብቁነትዎን ይመልከቱ በ doee.dc.gov/service/leadlinereplacement።

**የኪራይ ንብረት ባለቤቶች፣ አካራዮች፣ ኤጀንቶች፣ እና አስተዳዳሪዎች**

- የሊድ ይፋ ማድረጎች እና ሌሎች አስፈላጊ ቅጾች፣ ከሊድ-ነጻ የሥራ ልምምዶች፣ ማረጋገጫ፣ እና ስልጠናን በተመለከተ የዲስትሪክት ህጎችን ይከተሉ። የበለጠ ይማሩ በ፥ doee.dc.gov/lead።
- የፌዴራል ደንቦችን ይመልከቱ፣ የጥገና እና ቀለም መቀባት መረጃ፣ ቅጾች፣ እና ስልጠናን ያሳድሱ በ epa.gov/lead።



Lead Free KIDS for a Healthy Future
DEPARTMENT OF ENERGY & ENVIRONMENT
WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR